የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፴፯
አዲስ አበባ መጋቢት ፳፭ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No.37
ADDIS ABABA 3rd April, 2015

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፪/፳፻፯ ዓ.ም

የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓት·ና የማስረጃ ሕግን (ማሻሻያ) አዋጅ......................................ገጽ ፰ሺ፩፻፹፫

አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፪/፳፻፯ ዓ.ም

**የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ**

በተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓት·ና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፬/፲፱፻፺፯ ውስጥ ግልፅነት የጎደላቸውን ድንጋጌዎች ግልፅ በማድረግ ማሻሻል እና አዳዲስ ድንጋጌዎችን ማካተት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሙስና ወንጀልን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ውስጥ በሙስና ወንጀልነት እንዲካተቱ የተደረጉ የተወሰኑ የህዝባዊ ድርጅት· አካላት·ን በሥነ-ሥርዓት·ና በማስረጃ ሕጉም ማካተት· አስፈላጊ በመሆኑ፤

ሙስና ወንጀልን በሚመለከት· መረጃ የመሰብሰብ፣ የምርመራ፣ የክስ፣ የክርክር፣ በሙስና የተገኘ ሀብት· ወይም ተመጣጣኙን የማገድና የማስመለስ ሥራ ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት· አንቀፅ ፶፭(፩) መሠረት· የሚከተለው ታውጇል፡፡

CONTENTS

Proclamation No. 882/2015

The Revised Anti-Corruption Special Procedure and Rules of Evidence (Amendment) Proclamation……..
……………………………………………Page 8183

PROCLAMATION No. 882/2015

**A PROCLAMATION TO AMEND THE REVISED ANTI-CORRUPTION SPECIAL PROCEDURE AND RULES OF EVIDENCE PROCLAMATION**

WHEREAS, it is found necessary to clarify those unclear provisions and to include new provisions in the Revised Anti-Corruption Special Procedure and Rules of Evidence Proclamation No. 434/2005;

WHEREAS, it is necessary to include public organizations in the procedure and evidence laws as they are made part of the Revised Corruption Crimes Proclamation;

WHEREAS ,it is found necessary to ensure the speedy and effective gathering of information, investigation, prosecution and hearing of corruption offences and the injunction and retrieval of property obtained there from;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 9.95

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፪/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.ማሻሻያዎች**

የተሻሻለው ልዩ የፀረ-ሙስና የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፬/፲፱፻፺፯ እንደገና እንደሚከተለው ተሻሽሏል:-

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀፅ (፩) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፩) ተተክቷል፤

"፩/ 'የሙስና ወንጀል' ማለት የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፩/፪ሺ፯ የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል፤

፪/ የአዋጁ አንቀፅ ፪ ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተሸጋሽጎ ንዑስ አንቀፅ (፱) ሆኖ የሚከተሉት አዲስ ንዑሳን አንቀፆች (፭)፣ (፮)፣ (፯) እና (፰) ተጨምረዋል፤

"፭/ 'አዋጅ' ማለት የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፬/፲፱፻፺፯ ነው፤

፮/ 'ኮሚሽነር' ማለት የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ነው፤

፯/ 'ጠቋሚ' ማለት ተፈፅሟል ወይም ሊፈፀም ነው ብሎ ያመነውን የሙስና ወንጀል የሚመለከት መረጃ አግባብ ላለው አካል ወይም ለሌላ የፍትህ አካል፣ ለመንግስት መሥሪያ ቤት፣ ለመንግስት የልማት ድርጅት ወይም ለህዝባዊ ድርጅት የበላይ ኃላፊ ወይም በህግ ወይም በመመሪያ የሙስና ወንጀል ጥቆማን እንዲቀበል ኃላፊነት ለተሰጠው ሌላ አካል የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ሲሆን፣ ለእነዚህ ለተጠቀሱት አካላት ጥቆማ ባያቀርብም የሙስና ወንጀል የተፈፀመበትን ጉዳይ ኦዲት የሚያደርግ ወይም በኦዲት ተግባሩ ሙስና

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Revised Anti-Corruption Special Procedure and Rules of Evidence (Amendment) Proclamation No.882/2015."

**2. Amendments**

The Revised Anti-Corruption Special Procedure and Rules of Evidence Proclamation No. 434/2005 is hereby further amended as follows:

1/ Sub-article (1) of Article 2 of the Proclamation is deleted and is replaced by the following new sub-article (1):

"1/ corruption offenses" means corruption offences provided for by the Corruption Crimes Proclamation No.881/2015":

2/ The existing sub-article (5) of Article 2 of the Proclamation is renumbered as sub-article (9) and the following new sub-articles (5), (6), (7) and (8) are added:

"5/'Proclamation' means the Revised Anti-Corruption Special Procedure and Rules of Evidence Proclamation No. 434/2005;

6/ /'commissioner' means the commissioner of the Ethics and Anti-corruption Commission;

7/ 'informant' means any person who provides information, when he believes that corruption offences are committed, to appropriate organ or other justice organs, to the heads of public office, public enterprise or public organization or to anyone who has the duty to investigate crimes of corruption based on laws or directives and includes an auditor who audits matters relating to offences of corruption or an auditor who detects the commission of the offence of corruption in connection with the course of his

መፈፀሙን ያጋለጠ ኦዲተርን እና ጥቆማን የሚያጣራ ወይም የሚመረምር ሰውን ያካትታል፤

፰/ 'የበላይ ኃላፊ' ማለት አንድን የመንግስት መሥሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት በኃላፊነት የሚመራ ሰውን ወይም ምክትሎቹን ወይም ሚኒስትር ዴኤታዎችን ይመለከታል፤

፱/ 'ህዝባዊ ድርጅት' ማለት የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፩/፪ሺ፯ የተሰጠውን ትርጓሜ ይኖረል፤"

፫/ የአዋጁ አንቀፅ ፬ ንዑስ አንቀፅ (፩) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፩) ተተክቷል:-

"፩/ በሙስና ወንጀል የተያዘ ሰው በዋስ እንዲለቀቅ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፤ ሆኖም የተከሰሰበት ወይም የተጠረጠረበት ወንጀል ከአሥር ዓመት በላይ በሆነ ፅኑ እሥራት ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ አይችልም፡፡ ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩም እየተደመሩ ከአስር አመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትና ይከለከላል፡፡"

፬/ ከአዋጁ አንቀፅ ፯ ንዑስ አንቀፅ (፬) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፭) ተጨምሯል:-

"፭/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (፬) የተደነገገው ቢኖርም:-

ሀ) እነዚህ የሥነ-ሥርዓት ጉዳዮች የሙስና ወንጀሉን የማየት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት እንዲታዩ መደረጉ የተከሳሹን መብት የሚያጣብብ ወይም ማስረጃ እንዲጠፋ ምክንያት የሚሆን ወይም ተገቢ ላልሆነ ወጪ የሚዳርግ መሆኑን አግባብ ያለው

auditing duties, and anyone who inspects or investigates such offences;

8/ 'head' means any person who leads a public office, public enterprise or public organization, or his deputies or deputies of state ministers;

9/'public organization' shall have the meaning provided to it in the Corruption Crimes Proclamation No. 881/2015."

3/ Sub-article (1) of Article 4 of the Proclamation is deleted and is replaced by the following new sub-article (1):

"1/ Any arrested person for a corruption offence may apply to a court to be released on bail; provided, however, that an arrested person charged or suspected with a corruption offence punishable for more than 10 years shall not be released on bail. Where there are concurrent crimes punishable with more than 4 years and less than ten years and the punishment of the two crimes is more than ten years, the arrested person shall not be released on bail."

4/ The following new sub-article (5) is added after sub-article (4) of Article 7 of the Proclamation:

"5/ Notwithstanding the provisions of sub-article (4) of this Article:

a) the appropriate organ may decide to submit such matters to the nearest First Instance Court when it believes that submission of such procedural matters to the court having jurisdiction on corruption offences would affect the

አካል ካመነበት እንደ ሁኔታው በአቅራቢያው በሚገኝ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲታይ ሊወስን ይችላል፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀፅ በፊደል ተራ (ሀ) በተመለከተው አግባብ ጉዳዩ በቀረበለት ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን አግባብነት ወደአለው ፍርድ ቤት ይግባኝ መጠየቅ ይችላል። ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።"

፭/ የአዋጁ አንቀፅ ፰፣ ፱ እና ፳፱ ተሠርዘው በሚከተሉት አዲስ አንቀፆች ፰፣ ፱ እና ፳፱ ተተክተዋል:-

፰. "**መርህ**

፩/ የአዋጁ አንቀፅ ፲ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤት በወንጀል የተገኘ ማንኛውም ንብረት እና በወንጀል የተገኘው ንብረት ያፈራውን ንብረት ለማገድ ይችላል።

፪/ መርማሪ ወይም ዐቃቤ ህግ በወንጀል የተገኘ ማንኛውም ንብረት እና በወንጀል የተገኘው ንብረት ያፈራው ንብረት እንዲታገድ በቃለ መሀላ በተደገፈ መረጃ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል።

፫/ ለእግድ የሚቀርብ ማመልከቻ የወንጀል ክስ ከተመሰረተ በኋላ ወይም የወንጀል ክሱ ከመመስረቱ በፊት ሊቀርብ ይችላል።

፬/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (፩)፣ (፪) እና (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያለው አካል የበላይ ኃላፊ በፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ እስኪወጣ ድረስ ንብረቱ እንደሚባክን ሲያምንበት ለ፵፰ ሰዓት የሚፀና ጊዜያዊ የእግድ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል።

rights of the accused, cause loss of evidence or cause disproportionate cost;

b) the party aggrieved by the decision rendered by the court under paragraph (a) of this sub-article may lodge appeals to the appropriate court. The decision rendered by the appeal court shall be final."

5/ Articles 8, 9 and 29 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new Article 8, 9 and 29:

"8.**Principle**

1/ Without prejudice to Article 10 of this Proclamation, a court may issue a restraining order against any property acquired by the commission of corruption offence and fruits thereof.

2/An investigator or a prosecutor, by evidence supported by an affidavit, may, apply to the court for a restraining order against any property acquired by the commission of a criminal offence and the fruits of thereof.

3/An application for a restraining order may be made before or after the institution of the criminal proceeding.

4/Without prejudice to sub-articles (1), (2) and (3) of this Article, head of the appropriate organ may, when he believes that the property may be squandered, give a restraining order effective only for 48 hours pending the issuance of an order by a court of law.

**፱.ሌሎች ንብረቶች ስለሚታገዱበት ሁኔታ**

፩/በሙስና ወንጀል የተገኘ ለመሆኑ መረጃ ባይቀርብም ምርመራ በተጀመረበት ወይም ክስ በቀረበበት የሙስና ወንጀል ተከሳሽ ያገኘው የማይገባ ጥቅም ወይም ያደረሰው ጉዳት ለመኖሩ በቃለ መሀላ ሲረጋገጥ በወንጀሉ ተገኘ ከተባለው የማይገባ ጥቅም ወይም ደረሰ ተብሎ ከሚገመተው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ በተከሳሽ፣ በትዳር ጓደኛው ወይም ከ ፲፰ ዓመት በታች በሆነ ልጁ ስም በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ ወይም ንብረት ወይም በእነዚሁ ሰዎች ስም ያለ ንብረት እንዳይሸጥ፣እንዳይለወጥ ወይም እንዳይተላለፍ ታግዶ እንዲቆይ በመርማሪ ወይም በዐቃቤ ህግ አቤቱታ ሲቀርብ ፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የሚሰጥ የእግድ ትእዛዝ ተጠርጣሪው በታገደው ንብረቱ የመጠቀም መብቱን አይነካም፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተደነገገው ቢኖርም ተጠርጣሪው በባንክ በተቀመጠው ገንዘብ ወይም ንብረት የመጠቀም መብት አይኖረውም፡፡ ሆኖም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ ፍርድ ቤቱ እንዲታገድ ከተደረገው ከዚሁ ገንዘብ ወይም ንብረት ውስጥ ተጠርጣሪው ሊጠቀምበት የሚገባ መጠን ወስኖ እንዲጠቀም ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

፬/ ተጠርጣሪው በተፈቀደለት የመጠቀም መብት ሲጠቀም በንብረቱ ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል ተብሎ ሲገመት መርማሪው ወይም ዐቃቤ ሕጉ ንብረቱን ከጉዳት ለመከላከል የሚጠቅም ትእዛዝ እንዲሰጥለት ፍርድ ቤቱን ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ በቀረበው ጥያቄ ላይ ተገቢ የሆነውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**9.Condition for Restraining other Properties**

1/ Notwithstanding that there is no evidence that the property is acquired as a result of the corruption offence, where an investigator or prosecutor made an application for a restraining order supported by an affidavit indicating that the suspect is enriched or others suffered damage as a result of the corruption offence being investigated or charged, the court may give a restraining order prohibiting the sale, assignment or transfer of any money or property deposited in any bank in the name of the suspect, his spouse or children under the age of 18 or any other property of such persons proportionate to the amount of enrichment by the suspect or damage suffered by others.

2/ The restraining order given according to sub-article (1) of this Article shall not affect the suspect's right of using such property.

3/ Notwithstanding the provisions of sub-article (2) of this Article, the suspect shall not have the right to use cash or property deposited in a bank. When compelling circumstances emerge, the court may allow the suspect to use the appropriate amount of such cash or other property.

4/ When the investigator or the prosecutor so applies, the court may give an order it deems fit to minimize the damages that may result when the suspect uses the property.

**፳፱.ንብረት ስለሚወረስበት ሁኔታ**

፩/ ተከሳሽ በሙስና ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ:-

ሀ)በሙስና ወንጀል የተገኘ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ንብረትና በወንጀሉ ከተገኘው ንብረት ያፈራው ንብረት ወይም በሙስና ወንጀሉ ከተገኘው ጥቅምና በወንጀል ከተገኘው ንብረት ያፈራው ንብረት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ማናቸውም የተከሳሹ ንብረት እንዲወረስ፣ ወይም

ለ) በወንጀሉ ምክንያት ለራሱ ያገኘው ጥቅም ባይኖርም ሌሎች ሰዎች ጥቅም ማግኘታቸው ወይም በግለሰብ፣ በመንግሥት ወይም በሕዝባዊ ድርጅት ጥቅም ላይ የደረሰ ጉዳት መኖሩ ከተረጋገጠ ሌሎች ሰዎች ካገኙት ጥቅም ወይም ደረሰ ተብሎ ከሚገመተው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የተከሳሽ ንብረት በማካካሻነት እንዲወረስ፣ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፪/ ለዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) አፈፃፀም የተከሳሹ ንብረት በሙስና ከተገኘው ጥቅም ወይም ከደረሰው ጉዳት ያነሰ እንደሆነ ወይም በተከሳሹ ስም የተመዘገበ ንብረት ያልተገኘ እንደሆነ ውሳኔው በተከሳሹ የጋራ ንብረት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፫/ ለዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) አፈፃፀም የተከሳሹ የጋራ ንብረት በተከሳሹ እና በሌላ ሰው ስም በጋራ የተያዘ ንብረት ወይም በህግ እንደ የጋራ ንብረት የሚወሰድ ንብረት ሲሆን በተከሳሹ የትዳር ጓደኛ ወይም ከ፲፰ ዓመት በታች ዕድሜ ባለው ልጁ ስም፣ ወይም በእነዚሁ በሁለቱ ስም በጋራ ያለ ንብረት የተከሳሹ የጋራ ንብረት እንደሆነ ይገመታል፡፡ ሆኖም የሚመለከተው ሰው

**29.Conditions for Confiscation of Property**

1/ Where the accused is found guilty of corruption offence, the Court shall give a confiscation order on:

a) property obtained from corruption offences or fruits thereof or any property proportionate to the benefits obtained there from;

b) property of the accused proportional to the benefit procured by another person or damage caused by corruption offences on private, public or State interest or advantage of public organization even where the accused has not obtained benefits for himself from such offence.

2/ For the application of sub- article (1) of this Article, where the value of the property of the accused is less than the benefit obtained, or the damage caused by corruption offence or where no property is registered in the name of the accused, the common property shall be confiscated.

3/ For the application of sub- article 2 of this Article, any property jointly owned by the accused and another person or property so considered by law, property in the name of the spouse or child under the age of 18 or both shall be presumed to be the common property of the accused; provided, however, that the concerned person may rebut such presumption by presenting an evidence

ንብረቱ ከተከሳሹ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው የግል ሀብቱ መሆኑን በግልፅ የሚያስረዳ ማስረጃ ለፍርድ ቤት በማቅረብ ይህን ግምት ማፍረስ ይችላል፡፡"

፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፴፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል:-

"፩/ ፍርድ ቤቱ ንብረት እንዲወረስ ያልወሰነ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ ፳፱ በተመለከተው መሰረት ንብረት የመውረስ ጥያቄ በዐቃቤ ህግ አመልካችነት ሊታይ ይችላል፡፡"

፯/ የአዋጁ አንቀፅ ፴፪ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ ፴፪ ተተክቷል:-

፴፪. <u>ንብረትን በፍትሐ ብሔር ክስ ስለማስመለስ</u>

፩/ በዚህ አዋጅ በአንቀፅ ፳፱ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በተለያየ ምክንያት ክሱ እንዲቋረጥ በመደረጉ ወይም በማንኛውም ሌላ ምክንያት የጥፋተኝነት ውሳኔ ባይሰጥም በሙስና የተገኘ ንብረት እና በወንጀሉ በተገኘው ንብረት ያፈራው ንብረት ወይም በወንጀል ከተገኘው እና ከተፈራው ንብረት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ዋጋ እንዲወረስ ለማድረግ ወይም በወንጀሉ ለደረሰ ጉዳት ማካካሻ የሚሆን ተመጣጣኝ ዋጋን ለማስከፈል አግባብ ያለው አካል በፍትሐ ብሔር ክስ ሊመሰርት ይችላል፡፡

፪/ አግባብ ያለው አካል ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (፩) ከተገለፀው ውጭ በማንኛውም ምክንያት በሙስና ወንጀል የተገኘ ንብረት እና በወንጀሉ በተገኘው ንብረት ያፈራው ንብረት ወይም በወንጀል ከተገኘው እና ከተፈራው ንብረት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ዋጋ እንዲወረስ ለማድረግ፣ ወይም በወንጀሉ ለደረሰ ጉዳት

to the court showing that such property is his personal property.

6/ Sub-article (1) of Article 31 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

"1/ Where confiscation of property is not ordered by the court, it may be entertained by the application of the prosecutor pursuant to Article 29 of the Proclamation."

7/ Article 32 of the Proclamation is deleted and is replaced by the following new Article 32:

"32. **<u>Recovery of Property by Civil Action</u>**

1/ Without prejudice to the provisions of Article 29 of this Proclamation, the appropriate organ may institute civil action for purposes of confiscation of property obtained through corruption offences, or fruits thereof, or property proportionate therewith, or property proportionate to the damage caused thereby even where the criminal proceedings were terminated or no conviction was obtained for any reason.

2/ The appropriate organ may institute a civil action in situations other than those mentioned under sub-article (1) of this Article for purposes of payment of compensation proportional to property obtained as a result of corruption offences, or fruits thereof, or property proportionate therewith, or property proportionate to the damage caused thereby.

ማካካሻ የሚሆን ተመጣጣኝ ዋጋን ለማስከፈል በፍትሐ ብሔር ክስ ሊመሰርት ይችላል፡፡

፫/ በሙስና ወንጀል የተገኘው ንብረት የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት፣ የህዝባዊ ድርጅት ወይም የሌላ ግለሰብ ንብረት ወይም ገንዘብ ከሆነ ይኸው ተቋም ወይም ግለሰብ በሙስና የተገኘው ንብረት ወይም ገንዘብ እንዲመለስ በፍትሐ ብሔር ክስ እንዲመሰርት አግባብ ያለው አካል ፈቃድ ሊሰጥ ወይም ሊወክል ይችላል፡፡ አግባብ ያለው አካል እነዚህ ተቋማት የሚመሰርቱትን ክስ በሚመለከት ውጤቱን ይከታተላል፡፡

3/ If the proceeds of corruption offence is the property of a government office, public enterprise or public organization or any individual, the appropriate organ may give its permission or delegate for organs or individual to initiate civil action against the suspected person for the recovery of the assets. The appropriate organ shall have the duty to follow up the result of such action by the other organs.

፰/ የአዋጁ አንቀፅ ፴፬ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ ፴፬ ተተክቷል፤

"፴፬. <u>ተመላሽ ስለሚሆነው የንብረት ወይም የጥቅም መጠንና ንብረቱ ለመንግስት ገቢ ስለሚሆንበት ሁኔታ</u>

፩/ ተከሳሹ በሙስና ወንጀል ያገኘው ንብረትና በወንጀል ከተገኘው ንብረት ያፈራው ንብረት ወይም ተመጣጣኙ፣ ወይም በወንጀሉ ካደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ንብረት ተመላሽ ይደረጋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) በተመለከተው መሠረት ተመላሽ የሚደረገው የንብረት መጠን ተከሳሹ ካገኘው ጥቅም ወይም ያገኛል ተብሎ ከሚገመተው ጥቅም ወይም ደረሰ ተብሎ ከሚገመተው ጉዳት በላይ መሆን ወይም መብለጥ የለበትም፡፡

8/ Article 34 of the Proclamation is deleted and is replaced by the following new Article 34:

"34. <u>The amount of Property or Benefit to be Recovered and the Manner of returning it to the Government</u>

1/ The defendant shall return the property acquired by the commission of the crime and the benefit derived from the property or the amount equivalent to it or the amount equivalent with the damage sustained by the commission of the crime.

2/ The amount of benefit to be returned according to sub-article (1) of this Article shall not exceed the benefit acquired or the amount that might be presumed to be realized or the damage sustained.

፫/ በፍርድ እንዲወረስ ውሳኔ የተሰጠበትን ንብረት አግባብ ያለው አካል በመረከብ ለመንግስት ያስረክባል። ንብረቱ ሙሉ በሙሉ የማይወረስ ሲሆን ወይም ከሌላ ንብረት ጋር ተዳብሎ የሚገኝ ሲሆን አግባብ ያለው አካል ንብረቱ በፍርድ አፈፃፀም መሠረት እንዲሸጥ በማድረግ ገንዘቡን ለመንግስት ገቢ ያደርጋል።”

፱/ የአዋጁ አንቀፅ ፴፮ ንዑስ አንቀፅ (፪) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፪) ተተክቷል:-

፪/ በቅድመ ክስ ሂደት ፍርድ ቤቱ፣

ሀ) ዐቃቤ ሕግና ተከሳሽ በዚህ ክፍል የተጣለባቸውን ግዴታዎች መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፤

ለ) በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ አንቀፅ ፻፴ መሠረት ለሚነሱ ጉዳዮች እልባት ይሰጣል፤

ሐ) ዐቃቤ ሕግ የተከሳሽን መልስ ከተመለከተ በኋላ ክስ ማሻሻያ መኖር ያለመኖሩን በመጠየቅ ያረጋግጣል፤ የሚሻሻል ሲኖርም ክሱን እንዲያሻሽል ዐቃቤ ህጉን ያዘዋል።

፲/ የአዋጁ አንቀፅ ፴፯ ንዑስ አንቀፅ (፬) ተሠርዟል።

፲፩/ የአዋጁ አንቀፅ ፵ እና ፵፩ ተሠርዘው ከአንቀፅ ፵፪ እስከ ፶፮ ያሉት ነባር አንቀፆች እንደ ቅደም ተከተላቸው ከአንቀፅ ፵ እስከ ፶፬ ሆነው ተሸጋሽገዋል።

፲፪/ በአዋጁ አንቀፅ ፵፬ ከንዑስ አንቀፅ (፫) (በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፲፩) እንደተሸጋሸገው) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀፆች (፬) እና (፭) ተጨምረዋል፤

3/ The appropriate organ shall collect the property on which confiscation order was given and hand it over to the Government. Where the property cannot be confiscated fully, or where it is merged with other property or happens to be accessory of other property, the appropriate organ shall have it sold legally and handover the proceeds of such sale to the Government.

9/ Sub-article (2) of Article 36 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (2):

2 / During the preparatory hearing the Court shall:

a) ensure that the prosecutor and the accused have discharged their duties in this Section;

b) give rulings on matters that arise under Article 130 of the Criminal Procedure Code;

c) after hearing the accused, ensure whether the prosecutor would make any changes to the charges when making changes to the charges is necessary, it gives an order to the prosecutor to this effect.

10/ Sub-article (4) of Article 37 of the Proclamation is deleted.

11/ Articles 40 and 41 of the Proclamation are deleted and the existing Articles from Article 42 to 56 are re-numbered as Articles 40 to 54, respectively.

12/ The following new sub-articles (4) and (5) are added after sub-article (3) of Article 44 of the Proclamation (as re-numbered under sub-article (11) of this sub-article):

፬/ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ ስልክ በመደወል ተገቢ ያልሆነ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ ወይም ምስክርን፣ ጠቋሚን፣ ባለጉዳይን፣ መርማሪን፣ ዐቃቤ ህግን ወይም ዳኛን ያስፈራራ ሰውን ማንነት እና አድራሻ ጉዳዩ የሚመለከተው የቴሌኮሙኒኬሽን አካል እንዲያሳውቀው አግባብ ያለው አካል የበላይ ኃላፊ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፭/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት የደዋዩን ማንነት እና አድራሻ እንዲያሳውቅ ጥያቄ የቀረበለት ጉዳዩ የሚመለከተው አካል የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ሳይዘገይ የተሟላ መረጃ ጥያቄውን ላቀረበለት አግባብ ላለው አካል መስጠት አለበት፡፡ መረጃውን አለመስጠት ወይም መረጃውን በተሟላ መልኩ አለመስጠት አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ያስጠይቃል ፡፡

፲፫/ የአዋጁ አንቀፅ ፶፩ ንዑስ አንቀፅ (፪) (በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፲፩) እንደተሸጋሸገው) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፪) ተተክቷል፤

፪/ እያንዳንዱ የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛውን ከቂም በቀል እርምጃ ለመከላከል የሚያስችለው ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

፲፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፶፪ (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፲፩) እንደተሸጋሸገው) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ ፶፪ ተተክቷል፤

፶፪.<u>የቂም በቀል እርምጃን ስለማገድ</u>

፩/ የቂም በቀል እርምጃ የተወሰደበት ሰው ሠራተኛ ከሆነ በአስተዳደሩ የተወሰደበት እርምጃ እንዲታገድለት አግባብ ላለው አካል አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

4/ The head of the appropriate organ may request the appropriate telecommunication's organ to divulge the identity and address of anyone who demands, through a telephone call to be paid an undue advantage, threatens a witness, an informant, an applicant, investigator or a judge.

5/ The appropriate head or employee to whom a request for divulging of the identity and address of the caller is directed as prescribed under sub-article (4) this Article shall provide such information without delay. Failure to provide information or providing incomplete information shall be punishable under the relevant criminal provisions.

13/ Sub-article (2) of Article 51 of the Proclamation (as re-numbered under sub-article (11) of this sub-article) is deleted and replaced by the following new sub-article (2):

2/ Every government office, government enterprise or public organization shall establish a procedure to protect its employees from reprisal.

14/ Article 52 of the Proclamation (as re-numbered under sub-article (11) of this sub-article) is deleted and replaced by the following new Article 52.

52.<u>Suspension of Reprisal Measures</u>

1/Where the person against whom a reprisal measure has been taken is an employee, he may apply to appropriate organ for a suspension of the reprisal.

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) አቤቱታ የቀረበለት አግባብ ያለው አካል አቤቱታውን ወዲያውኑ በመቀበል የቂም በቀል እርምጃ መኖር አለመኖሩን በማጣራት ተገቢነት ያለውን ትዕዛዝ መስጠት ይኖርበታል፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት አግባብ ያለው አካል በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ወገን አቤቱታውን በ ፷ ቀናት ጊዜ ውስጥ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አቤቱታውን ለፍርድ ቤት ካላቀረበ ተቀባይነት እንዳገኘ ተቆጥሮ ውሳኔው የፀና ይሆናል፡፡

፬/ አግባብ ያለው አካል የቂም በቀል እርምጃ በወሰደው ሰው ላይ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት የወንጀል ክስ የመሰረተ እንደሆነ በቀረበው ክስ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የእግድ ትእዛዙ እንደፀና ይቆያል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ለፍርድ ቤት በቀረበው አቤቱታ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ እንደፀና ይቆያል፡፡"

፲፭/ ከአዋጁ አንቀፅ ፶፬ (በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፲፩) እንደተሸጋሸገው) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀፆች ፶፭፣ ፶፮ እና ፶፯ ተጨምረዋል፤

፶፭.<u>የመቀጮ ቅጣት ተፈፃሚነት</u>

፩/በሙስና ወንጀል ጥፋተኝነቱ የተወሰነበትን የመቀጮ ቅጣት ተከሳሹ መክፈል ካልቻለ በወንጀል ህግ ሥነ-ሥርዓት መሰረት ፍርድ ቤቱ የሚወስዳቸው እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው አግባብ ያለው አካል ቅጣቱን ተከታትሎ

2/ The appropriate organ which has received the application in accordance with sub-article (1) of this Article shall examine the existence or none existence of reprisal measure and give forthwith an appropriate provisional ruling.

3/Any organ that received suspension order on the reprisal measure from the appropriate organ pursuant to sub-article (2) of this Article may lodge application to a court of law within 60 days; if the application is not lodged within this time limit, the order shall be presumed as accepted and be valid.

4/ Where the appropriate organ instituted a criminal charge against the person who has taken a reprisal measure, the suspension order shall remain in force until the case is disposed.

5/ The suspension order given pursuant to sub-article (2) of this Article shall remain valid until the court gives its final judgment on matters submitted to it in accordance with sub-article (4) of this Article.

15/ The following new Articles 55, 56 and 57 are added after Article 54 of the Proclamation (as re-numbered under sub-article (11) of this sub-article)

55.<u>Enforcement of Fines</u>

1/ Without prejudice to the measures provided for under the Criminal Procedure Code, where a person convicted of corruption offence is unable to pay the fines, the Court shall order the appropriate organ to ensure that the sentence

እንዲያስፈፅም ፍርድ ቤቱ ያዘዋል፡፡

፪/ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ትእዛዝ የተሰጠው አግባብ ያለው አካል መቀጮው ለመንግሥት ገቢ መደረጉን ያረጋግጣል፤ ገቢ ያልተደረገ ሲሆን ገቢ ስለሚሆንበት ወይም የማካካሻ እርምጃ ስለሚወሰድበት ሁኔታ አጥንቶ ለፍርድ ቤቱ ያቀርባል፤ ፍርድ ቤቱ በቀረበው ጥናት ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**፶፮.<u>በወንጀል ያለመከሰስ መብትን ስለማንሳት</u>**

ያለመከሰስ መብትን ስለማንሳት በሌሎች ህጎች የተደነገገው ቢኖርም የፌደራል ወይም የክልል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የበላይ ኃላፊ ለመመርመርና ለመክሰስ ስልጣን በተሰጠው ጉዳዮች ዙሪያ ያለመከሰስ መብት የማንሳት ጥያቄን እንደሁኔታው ጉዳዩን ለሚመለከተው የሕዝብ ተወካዮች ወይም የክልል ምክር ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**፶፯.<u>በፌደራልና በክልል የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች መካከል ስለሚኖር የሥራ ግንኙነት</u>**

፩/ ሙስናን መሸከም የማይችል ህብረተሰብ በመፍጠር፣ እንዲሁም የሙስና ወንጀልን በመከላከል፣ በመመርመርና በመክሰስ ረገድ የፌደራል እና የክልል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ተቋሞች በትብብርና በተደጋጋፊነት ይሠራሉ፡፡

፪/ የክልል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ተቋሞች በኮሚሽኑ በሚሰጣቸው ውክልና መሠረት የሙስና ወንጀል ጉዳዮችን ሲመረምሩና ሲከሱ ተጠሪነታቸው ለኮሚሽኑ ይሆናል፡፡

፫/ የፌደራል እና የክልል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ተቋሞች ለፀረ-ሙስና እንቅስቃሴው ስኬት፣ ሀገራዊ የፀረ-ሙስና ትግሉ

regarding such fines is enforced.

2/ The appropriate organ shall ensure that the fines are paid to the Government; where it is not fully settled it shall provide the court with proposals for its payment or for other compensatory measures, and the court shall give order based on the proposals.

**56.<u>Lifting of Immunities</u>**

Notwithstanding provisions in other laws regarding lifting of immunity, the Head of the Federal or Regional Ethics and Anti-Corruption Commission may request the House of Peoples' Representatives or State Council for the lifting of the immunity on matters that fall within its powers.

**57.<u>Relationship between Federal and Regional Anti-Corruption Commissions</u>**

1/The Federal and Regional Anti-corruption Commissions shall cooperate and support each other on all efforts to create a society that does not tolerate corruption as well as on matters of prevention, investigation and prosecution of corruption crimes.

2/Regional Ethics and Anti-Corruption Commissions shall be accountable to the Federal Ethics and Anti-Corruption Commission when they investigate and prosecute corruption offences based on the power delegated to them by the Commission.

3/Federal and Regional Ethics and Anti-Corruption Commissions shall establish a joint forum to design and

አቅጣጫዎችን ለመንደፍና ለመተግበር፣ እንዲሁም በጋራ ለሚያከናውኗቸው ተግባራትና የሚያከናውኗቸውን ተግባራት አፈፃፀም ለመገምገም የሚወያዩበት የጋራ ጉባኤ ያቋቁማሉ፡፡ ጉባኤው በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር የጋራ ጉባኤውን ይመራል፡፡

፬/ የጋራ ጉባኤው:-

ሀ) የጋራ የአሠራር ውስጠ ደንብ ያወጣል፤

ለ) ሙስናን በመከላከል፣በመመርመር፣ በመክሰስ እና መልካም ሥነ-ምግባርን በማስፈን ረገድ የሥራ እንቅስቃሴዎችን በመገምገም የልምድ ልውውጥ ያደርጋል፤

ሐ) የፀረ ሙስና ትግሉን የሚያጠናክሩ ጥናቶች የሚካሄዱበትን አቅጣጫ ይቀይሳል፤ በሚቀርቡ ጥናቶች ላይ ይወያያል፤ በጥናቶቹ መሰረት ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች እንዲወሰኑ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል ወይም እንደሁኔታውም ይወስናል፤ በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

መ) ሥራውን የሚያቀናጅለት ጽህፈት ቤት ይኖረዋል፡፡ ጉባኤው በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የጋራ ጉባኤው ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፤

፭/ የጋራ ጉባኤው ያስተላለፋቸው ውሳኔዎች መተግበራቸውን የጉባኤው አባላት በየበኩላቸው ይከታተላሉ፡፡

፮/ የኮሚሽኑ አካላትና የክልል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ተቋሞች በየአካባቢያቸው ስላለው የሙስና ወንጀል ሁኔታ እና

implement directions for the fight against corruption and to evaluate the activities as well as their performance. unless decided otherwise by the forum, the Commissioner of the Federal Ethics and Anti-Corruption Commission shall preside over the forum.

4/ The Forum shall:

a) issue procedural manuals to the joint actions;

b) Share experience of good practices regarding to the prevention, investigation ,prosecution and prevalence of ethical practices;

c) give directions for the conduct of research that strengthen the fight against corruption; deliberate on research outputs; submit to the appropriate organ in order to take measure based on the research output or decide as the case may be or verify the practical application;

d) have an office to coordinate its efforts; unless decided otherwise by the forum, the Federal Ethics and Anti-Corruption Commission shall serve as the office of the forum.

5/The respective members of the forum shall ensure the implementation of the decisions of the forum.

6/ Organs of the Commission as well as Regional Ethics and Anti-Corruption Commissions shall submit periodic statistical reports to the office of the

ስለተከናወነ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ በሚመለከት ስታቲስቲካዊ መረጃ በየጊዜው ለጋራ ጉባኤው ጽህፈት ቤት ያስተላልፋሉ፡፡

፲፮/ የአዋጁ አንቀፅ ፶፯ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ ፶፰ ተተክቶ፣ ነባሮቹ አንቀጾች ፶፰ እና ፶፱ እንደ ቅደምተከተላቸው አንቀፅ ፶፱ እና ፷ ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

፶፰.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተፈፀሙ ወንጀሎች በነባሩ የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ልዩ የስነ ስርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፬/፲፱፻፺፯ መሰረት ፍፃሜ ያገኛሉ፡፡

፫.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት ፳፭ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት



forum regarding crime of corruption and anti-corruption activities in their respective regions

16/ Article 57 of the Proclamation is deleted and is replaced by the following new Article 58 and the existing Articles 58 and 59 are renumbered as Articles 59 and 60 respectively.

"58.<u>Transitory Provisions</u>

Cases pending on the effective date of this Proclamation shall be finalized based on the Revised Anti-Corruption Special Procedure and Rules of Evidence Proclamation No. 434/2005.

3.<u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa this 3rd day of April, 2015.

MULATU TESHOME (Dr.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA